# <u>አድዋ አይታሰብ</u>

ታሪክ ከመውረስ : ያልታደላችሁ
እኔን ባኮሩኝ : አገር በቅላችሁ
ዘመን በመቁጠር : ተጎልታችሁ
አገር መሸጡ : ኩራት ሆኗችሁ
ስሜን አታንሱ : አድዋ እያላችሁ : :

የኔማ ልጆች : አድዋን ያስጠሩ
ልበ ሙሉዎች : ጅንን የኮሩ
ያልበገራቸው : እሾህ ቆንጥሩ
ያላዛላቸው : ጥማት ሀሩሩ
ለመድፍ : መትረየስ : ያልተበገሩ
ጠላትን በሰይፍ : እየመተሩ
አገር ያኮሩ : ታሪክ የሰሩ
መች እንደናንተ : ሸሎች ነበሩ
በፈሪ አንደበት : ዛሬ የሚጠሩ : :

የጊዜ ነገር : ሆኖ አቶ አይቀሬ
ከባለዝናር : ባለጎፈሬ
እንዳልነበረ : ውሎና አዳሬ
ባንጃ ከሃዲ : ስታጀብ ዛሬ
መች ያኮራኛል : እድሜ መቁጠሬ
አንገት ደፍቼ : በልጅ አፍሬ : :

በናንተ ህሊና : አድዋ ሲታሰብ
መተማ ቋራ : ተወስዶ አሰብ
ምነው ባትጠሩኝ : ባልንገበገብ
አታንሱት ስሜንም: አውጡኝ ከመዝገብ
በውርደት ካባ :እንዴት ልታሰብ: :

ያርበኛን ስጋ : እርም የበላችሁ
የተበከለ :ደም አጥንታችሁ
ያባት አይመስል : ሙያ ሥራችሁ
አድዋን ለማክበር :ከየት መጣችሁ
ሥሙን በከንቱ :ታረክሳላችሁ : :

ባህረ ነጋሽ :አረብ ሰፍሮበት
ያባትህ ቀዬ : ድርቡሽ ነግሶበት
ጋሻ ዝናሩ : ትኋን ፈልቶበት
ሥሜን አትጥራ : ልሸሸግበት
ቀን እስኪወጣ: ልተክዝበት : :

ታዛቢው